## የጊዜው ፡ እሳሳቢ ፡ ጉዳዮች ።

### ለአመክሮ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ ስለ ፡ መፍታት ።

(በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፻፲፪ ፡ ፪፻፯ — ፲፪ ፡ እና ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ቁ. ፪፻፲፭ — ፲፭ ፡ መሠረት ፡ ለአመክሮ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ ስለመፈታት — የመለቀቁ ፡ ሁኔታዎች — የመፈታት ፡ ትእዛዝ ፡ የመስጠት ፡ ሥልጣን — ትእዛዙ ፡ የሚሰጥበት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡)

### መ ግ ቢ ያ ።

በእስራት ፡ እንዲቀጡ ፡ የተፈረደባቸው ፡ እስረኞች ፡ የተፈረደባቸው ፡ የእስራት ፡ ጊዜ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ በሕግ ፡ በተወሰኑ ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ቋሚ ባልሆነ ፡ ውሳኔና ፡ በአመክሮ ፡ እንዲፈቱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፻፲፪ ፡ ተደንግጓል ። እንዲሁም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፯፡ መሠረት ፡ ለአመክሮ ፡ የመፍታት ፡ ትእዛዝ ፡ የሚሰጠው ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች፡ነው ። እንዚሀ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ፡ የሚከተሉትን ፡ ጥያቄዎች ፡ ይቀሰቅሳሉ ።

(፩) ለአመክሮ ፡ የመፍታት ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ባለ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ መሰጠት ፡ ይገባዋል ?

(፪) ትእዛዙን ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የትኛው ፡ ነው ?

(፫) ትእዛዙስ ፡ የሚሰጥበት ፡ ትክክለኛ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ምንድን ፡ ነው ?

### የመልቀቁ ፡ ሁኔታዎች ።

ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎች ፡ ተሟልተው ፡ ካልተገኙ ፡ ለአመክሮ ፡ የመፍታት ፡ ትእዛዝ ፡ አይሰጥም ። እነዚሀ ፡ ሁኔታዎች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፻፲፪ ፡ እና ፡ ፪፻፯ ፡ ተዘርዝረዋል ። እነሱም ፡ ሁለት ፡ ናቸው ። የመጀመሪያው ፡ እስረኛው በእስር ፡ የቆየበትን ፡ ጊዜና ፡ የፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ያስከተለውን ፡ የጉዳት ፡ ካሣ የሚመለከት ፡ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ የእስረኛውን ፡ ጠባይ ፡ መሻሻልንና ፡ መታረምን ፡ የሚመለከት ፡ ነው ።

(፩) (ሀ) ከሁሉ ፡ በፊት ፡ ተቀጪው ፡ ከተወሰነበት ፡ የእስራት ፡ ጊዜ፡ውስጥ ሁለቱን ፡ ሲሶ ፡ እንዲፈጽም ፡ ያሻል ፤ ቅጣቱ ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ እስራት ፡ በሆነ ፡ ጊዜም ፡ ተቀጭው ፡ ሀያ ፡ ዓመት ፡ በእስር ፡ እንዲቆይ ፡ ያሻል ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፻፲፪ (፩)) ።

(ለ) በተጨማሪም ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ ተቀጪ ፡ በሠራው ፡ ወንጀል ፡ ምክንያት ፡ ለደረሰው ፡ ጉድለት ፡ መጠገኛ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፤

በፍርድ ፡ የተወሰነበት ፡ ወይም ፡ ከተበዳዩ ፡ ጋራ ፡ የተስማማበት ፡ ካሣ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መጨረሻ ፡ ዐቅሙ ፡ እስከ ፡ ፈቀደ፡ድረስ ፡ እንዲከፍል ፡ (እንዲያረካ) ፡ ያሻል ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፯ ፡ (ለ) ) ።

(፪) (ሀ) ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ ተቀጪ ፡ ለአመክሮ ፡ መፈታት ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ ይኖርበታል ፤ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፯ ፡ ሰባተኛው ፡ መሥመር) ። ጠባዩ ፡ "በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሚያስገኝ ፡ ካልሆነ" (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፪ ፤ (፩) ) ፤ ማለት ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሳለ ፡ በሥራውና ፡ በአረማመዱ ፡ (በአኳኋኑ) ፡ "የተረጋገጠ ፡ የመሻሻል ፡ ማስረጃ" ፡ ካላሳየ ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፯ ፡ (ሀ) ) ፤ ተቀጪው ፡ ለአመክሮ ፡ መፈታት ፡ ተገቢ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይችልም ።

(ለ) "እርግጠኛ ፡ ውጤት ፡ የሚያስገኝ፡ መሆኑ ፡ ካልታመነ ፡ በቀር" ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፯ ፡ ከመጨረሻው ፡ ስምንተኛው ፡ መሥመር ) ፡ ለአመክሮ ፡ የመልቀቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለማይሰጥ ፡ እስረኛው ፡ እንዲለቀቅ ፡ የእስረኛው ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ ጠባዩ ፡ መልካም ፡ መሆን ፡ ብቻውን ፡ በቂ ፡ አይደለም ። በተጨማሪ ፡ ዐመሉና ፡ እንዲሁም ፡ ነፃ ፡ በተለቀቀ ፡ ጊዜ ፡ የሚተዳደርበት ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ ያስገኝ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ ሊያስገምት ፡ የሚችል ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፯ ፡ (ሐ) ) ። እስረኛውን ፡ ለሙከራ ፡ በመፍታት ፡የሚፈጠረው ፡ አሥጊ ፡ ሁኔታ ፡ ከተለቀቀ ፡ በኋላ ፡ እስረኛው ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ማግኘቱና ፡ አለማግኘቱ ፡ ወይም ፡ ከቤት ፡ ሰቦቹ ፡ እንደሚያገኘው ፡ የሞራልና ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታ ፡ መጠንና ፡ እነዚህን ፡ በመሳሰሉ ፡ ነገሮች ፡ መሠረት ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ ማለቱ ፡ አይቀርም ።

ለአመክሮ ፡ የመልቀቅ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጥ ፡ ተሟልተው ፡ መገኘት ፡ የሚገባቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ እነዚሁ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ብቻ፡ናቸው ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፪ (፪) ፡ የእስር ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ደንቦች ቁ. ፪፻፪ (፩) ፡ የሚፈጸምበትን ፡ አኳኋንና ፡ ዝርዝር ፡ ሁኔታዎች ፡ እንደሚወሰኑ፡ ማውሳቱ ፡ የታመነ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ በወንጀለኛ፡መቅጫ ሕጉ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ በላይ ፡ በተጨማሪ ፡ ወይም ፡ በመቃወም ፡ የሚያቀርቡት፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ሌለ ፡ የተረጋገጠ ፡ በመሆኑ ፤ የነሱ ፡ ለጊዜው ፡አለመኖር ፡ ለአመክሮ ፡ የመፍታት ፡ ትእዛዝን ፡ ለመንፈግ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ ሊቈጠር ፡ አይገባም ። እስረኛው ፡ ለመሻሻል ፡ የተረጋገጠ ፡ ማስረጃ ፡ ማሳየቱን ፡ በትክክል ፡ መመጠኛ ፡ መሠረት ፡ ለመወሰን ፡ እንዲያስችል ፡ እነዚህ ፡ የእስር ፡

ቤት ፡ ደምቦች ፤ ለምሳሌ ፤ ለመፈታት ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ለመገኘት ፡ እስረኛው፡ሊያ ሳየው ፡ የሚገባውን ፡ የመጨረሻ ፡ እነስተኛ ፡ ውጤት ፤ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፻፲፪ (፩) ፡ ሁለተኛው ፡ ረድፍ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ የሚቆይበትን ፡ ጊዜ ፡ መጠንና ፡ የሚኖርበትን ፡ ሁኔታ . . . ወዘተርፈ ፤ ይደነግጉ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ የእስረኛው ፡ መሻሻል ፡ ሊወሰን ፡ የሚቻልበት እላይ ፡ እንደ ፡ ጠቀስነው ፡ ያለ ፡ መመጠኛ ፡ ከሌለ ፡ እስረኛው ፡ እልታረመም ፡ ለአመክሮ ፡ መፈታትም ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ አልተገኘም ፤ ማለት ፡ አይደለም ፤ ሊሆ ንም ፡ አይችልም ።

## የመፍታት ፡ ትእዛዝ ፡ የመስጠት ፡ ሥልጣን ።

ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በስተቀር ፡ ለአመክሮ ፡ የመፍታት ፡ ትእዛዝ ፡ የመስጠት ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡ ባለሥልጣን ፡ የለም ። በመፈጸም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ፍርድ ፡ ማሻሻል ፡ የሚጠይቅና ፡ በፍርድ ፡ ያለቀ ፡ ነገርን ፡ የሚነካ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ መሳይ ፡ ትእዛዝ ፡ በሥነ ፡ ፍጥረቱ ፡ አዲስ ፡ የዳኝነት ፡ ውሳኔን ፡ የሚጠይቅ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ለአመክሮ ፡ ለመፍታት ፡ ፍጹም ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ቢያገ ኘው ፡ የወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ እስረኛ ውን ፡ ለሙከራ  ጊዜ ፡ መፍታት ፡ አይገባውም ። የወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ተግባር ፡ በጉዳይ ፡ የመፍታት ፡ ትእዛዝ ፡ መስጠት ፡ ተገቢ፡መሆ ኑን ፡ ወይም ፡ አለመሆኑን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ምክር ፡ ማቅረብ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የጉ ዳዩ ፡ ውሳኔ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የግል ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ የመንግሥት፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖችም ፡ ቢሆኑ ፡ እንኳ ፡ ስለ ፡ እስረኛው ፡ መፈታት ፡ በሚደረገው ፡ ውሳኔ ፡ የሚያገባቸው ፡ ነገር ፡ የለም ። ከዚህ ፡ የተለየ ፡ መላ ፡ በሕገ፡ መንግሥቱ ፡ ቁ. ፲፲ ፡ የጸደቀውን ፡ የሥልጣን ፡ ክፍያ ፡ መሠረተ — ሐሳብ ፡ የሚቃ ወም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ በመሠረታቸው ፡ የተለያዩ ፡ ሁለት ፡ እርምጃዎችን ፡ ማለት ፡ ለአመክሮ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ መፍታትንና ፡ ምሕረትን ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ማጢቃ ለል ፡ ይሆናል ።

ለአመክሮ ፡ የመፍታት ፡ ሥልጣን ፡ ስለአለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ቁ. ፪፻፲፯ ፡ (፩) ፡ እና ፡ (፪) ፡ (ሠ) ፡ "የቅጣቱን ፡ ፍርድ ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ራሱ ፡ ትእዛዙን ፡ ይሰጣል" ፡ ይላል ። የተባለው ትእዛዝ ፡ በነዚያው ፡ የቅጣቱን ፡ ፍርድ ፡ በሰጡት ፡ ዳኞች ፡ እንዲታዘዝ ፡ ግዴታ ፡ የለም ። የቅጣቱን ፡ ፍርድ ፡ የሰጡት ፡ ዳኞችም ፡ ቢሆኑ ፡ እስረኛው ፡ ለመለቀቅ ፡ ተገቢ ፡ መሆኑንና ፡ አለመሆኑን ፡ ለመወሰን ፡ ስለ ፡ እስረኛው ፡ እምብዛም ፡ የሚ ያውቁት ፡ ነገር ፡ ስለሌለ ፤ ይህን ፡ መሳይ ፡ ግዴታ ፡ ያልተደነገገበት ፡ ምክንያት ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ተፈላጊው ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ለአመክሮ ፡ መፍታት ፡ ማመልከቻ ፡ በቀ

ረበ ፡ ወቅት ፡ የተሰየሙት ፡ ዳኞች ፡ የትኞችም ፡ ቢሆኑ ፡ በአመክሮ ፡ እስረኛውን ፡ ለመፍታት ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ተሟልተው ፡ ለመገኘታቸው ፡ የወህኒ ቤት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሚያቀርቡት ፡ ማስረጃ ፡ የመጨረሻውን ፡ ፍርድ ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያጠግብ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## የመፍታት ፡ ትእዛዝ ፡ የሚሰጥበት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ቁ. ፪፻፲፩ (፩) ፡ መሠረት ፡ እስረኛው ፡ ራሱ ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አማካይነት ፡ ካላመለከተ ፡ ወይም ፡ በቀጥታ ፡ የወህኒ ፡ ቤቱ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ካላመለከቱ ፡ በስተቀር ፡ ለአመክሮ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ የመፍታት ፡ ትእዛዝ ፡ አይሰጥም ። እስረኛው ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አማካይነት ፡ ሲያመለክት ፡ አመልካቹ ፡ እንዲፈታ ፡ ባለሥልጣኖቹ ፡ የማይስማሙ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ (ያልተስማሙ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ማድረግ ፡ የሚገባቸው ፡ ማመልከቻው ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚታይበት ፡ ወቅት ፡ የማይስማሙበትን ፡ ምክንያት ፡ መግለጽ ፡ ነው) ፤ ማመልከቻውን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የግድ ፡ ማስተላለፍ ፡ አለባቸው ። አንድ ፡ እስረኛ ፡ እንዲለቀቅ ፡ የሚስማሙ ፡ ሲሆንም ፡ ራሳቸው ፡ ነገሩን ፡ እንዣሥተው ፡ የመጀመሪያውን ፡ እርምጃ ፡ መውሰድ ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ዘንድ ፡ የተለመደ ፡ ነው ። አመልካቹ ፡ የትኛውም ፡ ቢሆን ፡ ምንም ፡ አይደል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እስረኛው ፡ የሚለቀቅባቸው ፡ ምክንያቶች ፡ በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ የግድ ፡ መገለጽ ፡ አለባቸው ። በተረፈም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፻፲፪ ፡ መሠረት ፡ የሚረቀቀው ፡ ደንብም ፡ የማመልከቻውን ፡ ቅጥና ፡ በላዩ ፡ የሚገለጠውን ፡ ሙሉ ፡ ነገር ፡ ምናልባት ፡ ይወስን ፡ ይሆናል ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ማመልከቻው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፲፯ ፡ (፪-፭) ፡ መሠረት ፡ ይወሰንና ፡ የተፈቀደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ (የሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ከፈለገ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በማቅረብ ፡ ማመልከቻው ፡ እንዳይፈቀድ ፡ ለመቃወም ፡ መቻሉን ፡ አስተውል) ፤ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ ይሠራባቸዋል ።

፩ኛ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሁለት፡ ዓመት፡ ያላነሰ ፡ ከአራት ፡ ዓመት ፡ ያልበለጠ ፡ የአመክሮ ፡ ጊዜ ፡ <u>የግድ</u> ፡ መወሰን ፡ <u>አለበት</u> ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፱፡ ሁለተኛው ፡ ረድፍ) ። ለአመክሮ ፡ መፍታት ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ሳይነሣ ፡ በፊት ፡ ይህ ፡ የሙከራ ፡ ጊዜ ፡ ካላለቀ ፡ በቀር ፡ ቅጣቱ ፡ ተሟልቶ ፡ እንደተፈጸመ ፡ አይቈጠርም ።

፪ኛ ፤ እስረኛው ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ለመመለስ፡ ያለውን ፡ ዝንባሌ ፡ ለማሳነስ ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የጠባይ ፡ አመራር፡ ደንብ ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩ

ትን ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፲ (፩) ) ፤ ማለት ፡ በወንጀ ለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፱ ፡ የተመለከቱትን ፡ ዐይነት ፡ ደንቦች ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ። የማያስፈልጉም ፡ ሆነው ፡ ባገኛቸው ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ቤቱ ፡ እነዚህን ፡ ደንቦች ፡ ላይጠቀምባቸው ፡ ይችላል ።

ተለቃቂ ፡ እስረኞችም ፡ ለነሱው ፡ ሲባል ፡ በአንድ ፡ ዐይነት ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ቢሆኑ ፡ ደግ ፡ ነው ። ይህን ፡ ዐይነቱም ፡ ቁጥጥር ፡ ለወትሮው ፡ በአንድ ፡ የጠባቂ ነት ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ አስተዳዳሪ ፡ (ባልደረባ) ፡ ወይም ፡ በበጎ ፡ አድራጎት ማኅበሮች ፡ ተቈጣጣሪነትና ፡ መሪነት ፡ ይከናወናል ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ቁ. ፪፻፲ (፪) ) ። የዚህን ፡ ዐይነት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ወይም ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ማኅ በሮች ፡ አገልግሎት ፡ ለጊዜው ፡ አለመኖር ፡ እስረኞቹን ፡ ላለመፍታት ፡ እንደ ፡ ምክንያት ፡ ሊቈጠር ፡ አይገባውም ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፲ (፪)፡ ይህ ፡ የጥንቃቄ ፡ ሥርዐት ፡ ሊፈጸም ፡ የማይቻልበት ፡ ምክንያት ፡ ካጋጠመና ፡ ጠቃሚነት ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ ከታወቀ ፡ ተለቃቂው፡ ከዚህ ፡ ደንብ ፡ አፈጻጸም ፡ ውጭ ፡ ሊሆን ፡ እንደሚችል ፡ ለይቶ ፡ ስለሚያዝ ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ እስረ ኛውን ፡ አልፈታም ፡ ማለት ፡ ሕጉን ፡ መቃወም ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ ሕጉ ፡ ተለ ቃቂ ፡ እስረኞችን ፡ ለመጠበቅና ፡ ለመቈጣጠር ፡ የሚያቅት ፡ ሊሆን ፡ እንደሚችል፡ የተገነዘበው ፡ ቢሆን ፤ እስረኛውን ፡ ለአመክሮ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ ለመፍታት ፡ ግን ፡ እንቅፋት ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ አልገመተውም ። እስረኛው ፡ እንዲፈታ ፡ ሲፈ ቅድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ "የሙከራውን ፡ ውጤት ፡ ፍሬ ፡ ለማስገኘት ፡ የሚችል ፡ ለዚሁ ፡ ተገቢ ፡ የሆነውንና ፡ ይህንን ፡ የመሳሰለውን ፡ ሌላውን ፡ የመልካም ፡ ጠባይ ፡ አመራርን ፡ ደንብ" ፡ ሊያዝ ፡ እንደሚችል ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፱ ፡ እና ፡ ፪፻፲ ፡ ስለተገለጸ ፡ እላይ ፡ የገለጥነው ፡ መላ ፡ ምክንያት ፡ ስውር ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ቀጥታ ፡ መጠባበቅ ፡ ሊደረግ ፡ የማይቻል ፡ ቢሆን ፡ ለምሳሌ ፡ በፍርድ ፡ የተለቀቀው ፡ እስረኛ ፡ በየተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወይም ፡ ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ እንዲቀርብ ፡ ከማዘዝ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ተለቃቂው ፡ እስረኛ ፡ በመ ልካም ፡ ጠባይ ፡ መቆየት ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ የጠባቂነትን ፡ ተግባር ፡ ለማከ ናወን ፡ ታማኝ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ዘመድ ፡ ቃል ፡ እንዲገባ ፡ ከመጠየቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ የሚያግደው ፡ ነገር፡ የለም ። በሌላ፡ አነጋገር ፡ ደግሞ ፡ ለአመክሮ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ የመፍታትን ፡ ዓላማ ፡ ተቃራኒ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የእስረኛ ፡ ጠባይ ፡ ለማሻሻል ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ማንኛውንም ፡ ዐይነት ፡ ግዴታ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደገመተው ፡ ለመጠየቅ ፡ ፍጹም ፡ መብት ፡ ስለ ፡ አለው ፡ ጠባቂነት ፡ ከተሰጠው ፡ አስተዳዳሪ ፡ (ባልደረባ) ፡ ወይም ፡ ከበጎ ፡ አድራጎት ፡ ማኅበሮች ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ መጠበቂያ ፡ ዘዴዎች ፡ ለመጠቀም ፡ የሚያስችል ፡ ሰፊ ፡ ስፍራ ፡ በሕጉ ፡ ተመልክቷል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በ(፩) ፡ እና ፡ በ(፪) ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተጠቀሱትን ፡ የእስር ፡ጊዜና ፡ ካሣን ፤ እንዲሁም ፡ የተቀጪውን ፡ ጠባይ፡ የሚመለከቱ ፡ ሁኔታዎች ፡ ጐድለው ፡ ካልተገኙ ፡ በስተቀር ፡ ለአመክሮ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ ለመፈታት ፡ የቀረበውን ፡ ማመልከቻ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማሰናበት ፡ እንደ ፡ ማይገባው ፡ ጥርጥር ፡ ሊኖር ፡ አይ ችልም ። ከዚህ ፡ በወጡ ፡ ምክንያቶች ፡ የተነሣ ፡ ማመልከቻው ፡ እንዲወድቅ ፡ የ ሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ ሁሉ ፡ ከሕግ ፡ ውጪ ፡ እንደሆነ ፡ መቈጠር ፡ አለበት ። ለመ ፈታት ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ እስረኛ ፡ የተጠቀሱት ፡ የመጠባበቂያ ፡ ድርጅቶች ባለሙኖራቸው ፡ የሚገባውን ፡ መነፈግ ፡ የለበትም ። ጥፋተኛውን ፡ ስለመጠባ በቅ ፡ ፓርላማ ፡ ሲደነግግ ፡ የነበረውም ፡ ዓላማ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደ ፡ አጋጠመው በየጊዜው ፡ በሚወስነው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴዎች ፡ ፍጻሜ ፡ ሊያገኝ ፡ ይችላል ።